አኃዝ

አኃዝ ማለት መጀመሪያ ጥንት ማለት ነው፤ አኃዝ ለመላው ቁጥር ሁሉ ጠቅላይ ስም ነው፤ ከባለቤት በፊት እየገባ የማነስንና የመብዛትን ምስጢር ይገልጻል፣ ባለቤት ሲኖር ቅጽል ፤ባለቤት ከሌለ በቂ እየሆነ ይነገራል፣

የአኃዝ አይነቶች አምስት ናቸው እነሱም፡-

፩፣ መደባዊ ቁጥር

፪፣ ሕጋዊ ቁጥር

፫፤ ክፍላዊ ቁጥር

፬፣ ዕጽፋዊ ቁጥር

፭፣ መድብላዊ ቁጥር ይባላሉ

1/መደባዊ ቁጥር

መደባዊ ቁጥር የተበታተኑትን ነገሮች ሁሉ አሰሮና ሰብስቦ የሚያሳይ የጅምላ ቁጥር ነው ከአንድ እስከ ዐሥራ ዘጠኝ ያሉት ቁጥሮች በተባዕትና በአንስተ ጾታ ተለይተው ይነገራሉ። ከኺያ በላይ ቁጥሮች ግን ወንድና ሴት ሳይለዩ ዕሥራ ፣ሠላሳ በማለት እስተባበሩ ይሄዳሉ፣ የአጸጻፋቸው ሥርዓትም በአኃዝና በፊደል ነው።

ተባዕት		እንስት		
፩	አሐዱ	አንድ	አሐቲ	አንዲት
፪	ክልኤቱ	ሁለት	ክልኤቲ	ኹለት
፫	ሠለስቱ	ሦስት	ሠላስ	ሦስት
፬	አርባዕቱ	አራት	አርባዕ	አራት
፭	ኃምስቱ	አምስት	ኃምስ	አምስት
፮	ስድስቱ	ስድስት	ስሱ	ስድስት
፯	ሰብዐቱ	ሰባት	ሰብዑ	ሰባት
፰	ስምንቱ	ስምንት	ሰማኒቱ	ስምንት
፱	ተሰዐቱ	ዘጠኝ	ተስዑ	ዘጠኝ
፲	ዐሠርቱ	ዐሥር	ዐሥሩ	ዐሥር
፲፩	ዐሥራ ወአሐዱ	ዐሥራ አንድ	ዐሥር ወአሐቲ	ዐሥራ አንድ
፲፪	ዐሠርቱ ወክልኤቱ	ዐሥራ ሁለት	ዐሥር ወክልኤቲ	ዐሥራ ሁለት
፲፫	ዐሠርቱ ወሠለስቱ	ዐሥራ ሦስት	ዐሥር ወሠላስ	ዐሥራ ሦስት
፲፬	ዐሠርቱ ወአርባዕቱ	ዐሥራ አራት	ዐሥር ወአርባዕ	ዐሥራ አራ
፲፭	ዐሠርቱ ወኃምስቱ	ዐሥራ አምስት	ዐሥር ወኃምስ	ዐሥራ አምስት
፲፮	ዐሠርቱ ወስድስቱ	ዐሥራ ስድስት	ዐሥር ወስሱ	ዐሥራ ስድስት
፲፯	ዐሠርቱ ወሰብዓቱ	ዐሥራ ሰባት	ዐሥር ወሰብዑ	ዐሥራ ሰባት
፲፰	ዐሠርቱ ወስመንቱ	ዐሥራ ስምንት	ዐሥር ወሰማኒ	ዐሥራ ስምንት
፲፱	ዐሠርቱ ወተሰዐቱ	ዐሥራ ዘጠኝ	ዐሥር ወተስዑ	ዐሥራ ዘጠኝ

ዳግመኛም አሐድ አሐድ፤ክልኤት ክልኤቱ ፣ሠለስት፤ሠለስቱ፤እያለ በመንታ መንገድ ሲነገር አንድ አንድ፤ ሁለት ሁለት፤ሦስት ሦስት ተብሎ ይፈታል።

፳	ዐሥራ	ኻያ
፴	ሠላሳ	በቁሙ

፴	አርብዓ	አርባ
፶	ኃምሳ	አምሳ
፷	ስድሳ	በቁሙ
፸	ሰብዓ	ሰባ
፹	ሰማኒያ	ሰማኒያ
፺	ተሰዓ	ዘጠና
፻	ምእት	መቶ
፲፻	ዐሠርቱ ምእት	አንድ ሺሕ
፳፻	ዐሥራ ምእት	ሁለት ሺሕ
፴፻	ሠላሳ ምእት	ሦስት ሺሕ
፵፻	አርባዓ ምእት	አራት ሺሕ
፶፻	ኃምሳ ምእት	አምስት ሺሕ
፷፻	ስሳ ምእት	ስድስት ሺሕ
፸፻	ሰብዓ ምእት	ሰባት ሺሕ
፹፻	ሰማኒያ ምእት	ስምንት ሺሕ
፺፻	ተሰዓ ምእት	ዘጠኝ ሺሕ
፼	እልፍ	ዐሥር ሺሕ
፲፼	ዐሠርቱ እልፍ(አእላፍ)	መቶ ሺሕ
፳፼	ዐሥራ እልፍ	ሁለት መቶ ሺሕ
፱፼	አእላፋት	አንድ ሚልዮን
፲፱፼	ትእልፍት	ዐሥር ሚልዮን
፳፱፼	ዕሥራ ምእት እልፍ	ኻያ ሚልዮን
፱፱፼	ምእልፍት	መቶ ሚልዮን

ከዚህም በላይ አእላፈ አእላፋት ወትልፊተ አእላፋት የሚል ጽሑፍ ይገኛል፣ፍቹም ልክና መጠን የሌለው የብዙ ብዙ ማለት ነው፡

2 ሕጋዊ ቁጥር

የሕጋዊ ቁጥር መነሻ ራብዕ ፊደል ነው ፤በተባዕትና በአንስት ይነገራል፤

ተባዕት		አንስት	
አሐድ	አንደኛው	አሐቲ	አንደኛይቱ
ካልኣ	ሁለተኛው	ካልኣት	ሁለተኛይቱ
ሣልስ	ሦስተኛው	ሣልስት	ሦስተኛይቱ
ራብዕ	አራተኛው	ራብት	አራተኛይቱ
ኃምስ	አምስተኛው	ኃምስት	አምስተኛይቱ
ሳድስ	ስድስተኛው	ሳድስት	ስድስተኛይቱ
ሳብዕ	ሰባተኛው	ሳብዕት	ሰባተኛይቱ

ሳምን	ስምንተኛው	ሳምንት	ስምንተኛይቱ
ታስዕ	ዘጠነኛው	ታስዕት	ዘጠነኛይቱ
ዓሥር	ዐሥረኛው	ዓሥርት	ዐሥረኛይቱ

ምእላድን (ዊ፤ይ፤ት) ጨምሮ ሲነገርም፥-

<u>በተባዕት፥-</u> አሐዳይ፤አሐዳዊ፤ካልአይ፤ካልአዊ፤ሣልሳይ፤ሣልሳዊ፤

በእንስት፥-ቀዳማይት፤ቀዳማያዊ፤ካልአዪት፤ካልአዊት፤ሣልሳዪት ሣልሳዊት፤ እያለ በመንታ መንገድ ይነገራል፤ ፍቹ አንድ ነው አይለወጥም፤ በአሐዱና በክልኤቱ ምትክ የሚነገሩ ሌሎች የቁጥር ቃላትም አሉ። ከእነርሱም አሐዱን መስለው የሚነገሩ ዋሕድ፤ግዕዝ ፤አኃዝ፤ ጥንት፤ መሰረት፤ ቀዳም፤ቀዳሚ ሲሆን ክልኤቱን መስለው የሚነገሩ ደግሞ ካእብ ፤ዳግም፤ መንታ፤ዘውግ፤ዕምድ ናቸው፥

3 <u>ክፍላዊ ቁጥር</u>

ክፍላዊ ቁጥር የክፍሎችን መጠን በየድረጃው ለይቶ የሚያመለክት ነው፥ ይህም

1. መንፈቅ(ካልኢት)	እኩል ፤እኩሌታ
ሣልሲት	ሦስቲያ፤ሚሶ
ራብዒት	አራትያ፤ሩብ፤ርቦ
ኃምሲት	አምስቲያ፤ዐምሾ
ሳድሲት	ስድስቲያ
ሳብዒት	ሰባቲያ
ሳምኒት	ስምንቲያ
ታስዒት	ዘጠኒያ
ዓሥሪት	ዐሥሪያ፤ካሥር ንድ አንድ ማለት ነው፥

2/ በመደበኛነት ሲነገሩ ዕጽፍነትን የሚያመለክቱ ክፍሎች፥-

ምእሕዲት	አንድ እጅ
ምክልኢት	ሁለት እጅ
ምሥልሲት	ሦስት እጅ
ምርብዒት	አራት እጅ
ምኃምሲት	አምስት እጅ
ምስድሲት	ስድስት እጅ
ምስብዒት	ሰባት እጅ
ምስምኒት	ስምንት እጅ
ምትስዒት	ዘጠኝ እጅ
መዕሥሪት	ዐሥር እጅ

3/ በጥሬነት ሲነገሩ ሁኔታን የሚያመለክቱ ክፍሎች፦

እሕድና	አንደኛነት	ትእሕዲት	አንድነት
ክላኤ	ሁለተኛነት	ተክልእት	ሁለትነት
ሥላሴ	ሦስተኛነት	ትሥልስት	ሦስትነት
ርባዔ	አረተኛነት	ትርብዕት	አራትነት
ኀማሴ	አምስተኛነት	ትኀምስት	አምስትነት
ስዳሴ	ስድስተኛነት	ትስድስት	ስድስትነት
ሰባዔ	ሰባተኛነት	ትሰብዕት	ሰባትንት
ሰማኔ	ስምንተኛነት	ትስምንት	ስምንትነት
ትሳዔ	ዘጠነኛነት	ትስዒት	ዘጠኝነት
ዕሣሬ	ዐሥረኛነት	ትዕሥርት	ዐሥርነት

ሌላውን ሁሉ ያሳያል።

4/ ጊዜያትን የሚያመለክቱ ክፍሎች፦

እሕድ፤ምዕር	አንድ ጊዜ	እሕድ፤ምዕረ	በአንድ ጊዜ
ክልእ	ሁለት ጊዜ	ክልእ	በሁለት ጊዜ
ሥልስ	ሦስተ ጊዜ	ሥልሰ	በሦት ጊዜ
ርብዕ	አራት ጊዜ	ርብዓ	በአራት ጊዜ
ኃምስ	አምስት ጊዜ	ኀምስ	በአምስት ጊዜ
ስድስ	ስድስት ጊዜ	ስድሰ	በስድስት ጊዜ
ሰብዕ	ሰባት ጊዜ	ሰብዕ	በሰባት ጊዜ
ሰምን	ስምንት ጊዜ	ስምነ	በስምንት ጊዜ
ትስዕ	ዘጠኝ ጊዜ	ትስዐ	በዘጠኝ ጊዜ
ዕሥር	ዐሥር ጊዜ	ዕሥረ	በዐሥር ጊዜ እነደ ማለት ነው

4/ <u>መድበልዊ ቁጥር</u>

መድበልዊ ቁጥር ያለ አኃዝ የሚነገር ሰብሳቢና ከታች ቁጥር ነው፤ ስፍሩና ቁጥሩ ባልታወቀ ነገር ሁሉ በቅጽልነት አየገባ የማነስንና የመብዛትን መጠን ያመለክታል፥ይህም፦

ምሉእ	ንኡስ	መጠን
ፍጹም	ሕጹጽ	አምጣን
ብዙኅ	ኅዳጥ	ዐቅም
ንሕኑሕ	ውኅድ	
ዝሕዙሕ	ንስቲት	
ፍድፋድ	ሐቅ	የመሰለ ቃል ሁሉ ነው።